

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከጁላይ 21-31 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከኦገስት 1-10 እና ከኦገስት 11-20/2025 የሚኖረው የአየር

## ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በህር ዳር 45.4፣ 32.2፣ ደብረ ማርቆስ 32.3፣ ጅማ 51.5፣ መተሃራ 35.7፣ ነቀምት 40.8፣ አቦቦ 37.6፣ አዲግራት 60.8፣ አይራ 40.2፣ አማን 41.6፣ አምቦ 34.5፣ አንገር ጉቲን 30፣ አሶሳ 54.6፣ አዋሽ አርባ 78፣ አክሱም 38፣ አይከል 31.6፣ በደሌ 39.4፣ 60.2፣ በሂ 34.3፣ ቻግኒ 50.6፣ ጭራ 50.2፣ 47.4፣ ደብረ ወርቅ 34.1፣ ፉኙዶ 38.2፣ ጋምቤላ 127፣ ገዋኔ 52፣ ጊዳ አያና 34.1፣ 49.8፣ 38.4፣ ጊምቢ 40.5፣ ጉንዶ መስቀል 54.7፣ ካቺሴ 33፣ ቁሉምሳ 45.2፣ ላሊበላ 34.4፣ መሃል ሜዳ 42.3፣ አዳማ 44.3፣ 84.9፣ ፓዌ 32.1፣ 51.4፣ ሰኮሩ 30.6፣ ሰንቃጣ 34.2፣ 32.4፣ ሽሬ 40፣ ሾላ ገበያ 30፣ 36.6፣ ሲሪንቃ 34.5፣ ወገልጤና 37.1፣ ወረኢሉ 42፣ የትኖራ 30.8፣ አባይ ሸለቆ 39.8፣ 31.2፣ 36.5፣ 36.4፣ 41.2፣ 37.8፣ 45.3፣ አቦ ሞሪንጋ 45.2፣ 65.2፣ አዲስ አለም 31፣ አዲስ ዘመን 33.2፣ አዲ አርቃይ 80.4፣ 75.8፣ 77.7፣ 80፣ 81.5፣ 75.7፣ 75፣ 70፣ 72.5፣ 71.5፣ 72.8፣ አታንጎ 48.6፣ ቡሬ 30፣ ደበረ ሲና 59.7፣ ደጋን 38.8፣ ደንገጎ 30.4፣ ደራ 45፣ 32፣ 55.5፣ 40፣ 60.5፣ 45.5፣ 65፣ 75፣ 45.5፣ ዲንሾ 41፣ ፈረስ ቤት 38.1፣ 34.6፣ ጋሻና 61፣ 46፣ ጊሸ ራቢለ 66.7፣ ጉጉፍቱ 36.8፣ 35.6፣ ሃይቅ 40.5፣ ሃሮ 30.2፣ 30፣ 50.1፣ 40.2፣ 30፣ ሁንቲ 32.5፣ ጅሁር 49.8፣ ካራሚሌ 48፣ ቅዳሜ ገበያ 48.6፣ 56.8፣ ኩሚ 33፣ ማርዬ 40.7፣ ማይ ሃነሲ 64.6፣ መከነ እየሱስ 33.7፣ ሞላሌ 31.4፣ 36.3፣ ሙጊ 32.7፣ ኖፓ 35፣ ኦሞ ናዳ 32.6፣ ሸበል በረንታ 35.6፣ ትንሹ ሚጢ 35.9፣ ዉቅሮ 36፣ 30፣ ዉልበርግ 53፣ ያንፋ 40.5፣ 59.9፣ ያዮ 36.1፣ መንደር11 33.5፣ ስልጋ 39.4፣ ደዋ 32.1፣ስልሳ 32.2፣ እንዲሁም ተላላቅ 36.2፣ 48.6፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በ82 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.1-127 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ

አከባቢዎች መካከል ጋምቤላ፣ አዳማ፣ አዲ አርቃይ፣ አዋሽ አርባ፣ ደራ፣ ጊሸርቤል፣ አቦ ሞሪንጋ፣ ማይ ሃንሲ፣ ጋሸና፣ አዲግራት፣ በደሌ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከጁላይ 21-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


Ethiopian Meteorology Institute

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ እና የጋቢ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ61-830 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-11 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ የምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሓረርጌ ዞኖች፤ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎ፤ ማኦ ኮሞ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ፋንቲ፣ አዉሲ፣ና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ጥቂት የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ ከ31-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅና ምዕራብ ሓረርጌ፣ ከአማራ ክልል ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምምራቅ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል ኤሊዳር፣ ሰመራ፣ ገዋኔ፣ አይሻ፣ አዋሽ አርባ፣ ጎዴ፣ ድሬ ዳዋ፣ መተሃራ፣ መተማ፣ ቀበሪ ዳሀር፣ መኢሶ፣ ጭፍራ፣ ዳሊፋጊ፣ ፉኙዶ፣ ሻዉራ፣ ጪፋ፣ ጋምቤላ፣ ኑራ ኤራ፣ አቦቦ፣ ባቲ፣ ሲሪንቃ፣ ሸርቆሌ፣ ኮምቦልቻ፣ ላሬ እና አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 32.4 እስከ 45.8 ዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል፡

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የመጨረሻ የጁላይ አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የነበረው እርጥበት አሰቀድመው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች፣ በጁላይ መጨረሻ የሚዘሩ ሰብሎችን ለመዝራትና፣ እንዲሁም ከኤፕሪል ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ የውሃ ፍላጎትን ለማሻሻል፣ ለግጦሽ ሳርና ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡


በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ያለው ዝናብ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት እንዲሁም የመሬት አቀማመጣቸው ተዳፋታማ በሆኑ በአሪ ዞን ደቡብ አሪ ወረዳ ከመር ቀበሌ በተፈጠረዉ የመሬት ናዳ ምክንያት በሰው ህይወት እና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል። በተጨማሪም በረዶ ቀላቅሎ ከጣለው ከባድ ዝናብ ጋር በሰሜን ሸዋ በክንብቢት እና በመሃል ሜዳ በሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳስከተለ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

### 1.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁላይ ሶስተኛ አስር ቀን በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ መረብ ጋሽ፣ አፋር ደናክል፣ በላይኛው አዋሽ፣ በላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ እና በጥቂት ላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በላይኛው እና በመካከለኛው አባይ እና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው እንዲሁም በመካከለኛው አዋሽ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መጎልበት ጥሩ አስተዋፅዖ እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ ታችኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሆነው ቆይተዋል (ካርታ 5) ።





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2 መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በኦገስት ወር ውስጥ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የኦገስት ወር ከተቀሩት የክረምት ወራት በተሻለ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን አካቶ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ወር ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን በምዕራብ አጋማሽ በአብዛኛው የሀገሪቱ ሥፋራዎች ላይ ከ200-400 ሚ.ሜ እና በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከ400 ሚ.ሜ በላይ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ18-30 ለሚደርሱት ቀናት ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ከ6-20 ቀናት ያህል እስከ 300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በይበልጥ ይጠናከራሉ፡፡ በመሆኑም የክረምቱ ዝናብ በስርጭትም ሆነ በመጠን በተሻላ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ላይ ከፍተኛ ጥንካሬ የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡ ፡ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡


## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በኦገስት የመጀመሪያው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በሚቀጥሉት አስር ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | የምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | የዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ እና ባስኬቶ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ጋሞ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.4 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በኦገስት የመጀመሪያው አስር ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኚዶ አከባበዎች ላይ ከ30.2 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

በመጪዎቹ የኦገስት ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## 2.6 እ.አ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ሰሜን ምስራቅ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያላዉ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፤ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ ትግራይ፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ውስጥ የእርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት በቂ እርጥበት መኖር<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በእርሻ ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተት<br>• የአረም መስፋፋት | • ማሳ ላይ የተኛ ውሃን ከማሳ በማንጣፈፍ ማስወገድ<br>• የአፈር መሸርሸር ስጋትን ለመቀነስ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>• አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ የወላይታ፣ ጎፋ እና ባስኬቶ፣ የማሂ፣ ሀሪ፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት በቂ እርጥበት መኖር<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት<br>• የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ሰብሎች ባልተዘሩባቸዉ አካባቢዎች የሚገኘዉን እርጥበት በመጠቀም ለመዝራት | • ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር<br>• የአረም መስፋፋት | • ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት<br>• የአፈር መሸርሸር ስጋትን ለመቀነስ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>• አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |
| ምስራቅ ሸዋ፣ የምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | ሰብሎች ባልተዘሩባቸዉ አካባቢዎች የሚገኘዉን እርጥበት በመጠቀም ለመዝራት ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር ሰብሎች ባልተዘሩባቸዉ አካባቢዎች ሰብሎችን መዝራት |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖችች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎችን መሰብሰብ |

## 2.7 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የኦገስት የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ያገኛሉ። ይህም ሁኔታ በተፋሰሶች ላይ እና በተለያዩ ግድቦች ላይ ያለውን የውሃ አቅም የሚያጎለብት ሲሆን፣ በተለይም አልፎ አልፎ ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ እንዲሁም ወንዞች ከልካቸው በላይ መጨመር በተጨማሪም በላይኛው ተፋሰሶች ላይ በሚነሱ ወንዞች አማካኝንት በታችኛው ተፋሰሶች ላይ ጎርፍ የማስከተል ዕድል ይኖረዋል። በመሆኑም በወንዝ ዳርቻ፣ በረባዳማ እና ረግረጋማ የሚኖሩ ማህበረሰብ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ሊኖር የሚችለው አደጋ ለመቀነስም ሆነ መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ተዘርዝረዋል።፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው<br><br>አባይ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ ባሮ አኮቦ፣ አሞ ጊቤ፣ አዋሽ ፣ ላይኛው እና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ደዋ | ከመካከለኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ እርጥበት | • የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መጨመር<br>• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መጨመር<br>• የከርሰ ምድር የውኃ ከፍታን መሻሻል<br>• የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን መጨመር | • የቅፅበታዊ ጎርፍ ስጋት መጨመር<br>• የወንዞች ከልካቸው በላይ መሙላት<br>• በውሃ መያዣዎች ላይ የደለል ስጋት መጨመር<br>• የፍሳሽ መውረጃዎች በደለል እንዲሁም በጠጣር ቆሻሻ መዘጋት | • የጎርፍ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት<br>• የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• ፍሳሽ ሊዘጉ የሚችሉ ቆሻሻዎች በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ<br>• ወራጅ ውሀን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር<br>• ለጎረፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች ላይ ቅርብ ክትትል ማድረግ<br>• የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችን እና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው መካከለኛው እና የታችኛው<br>• ገናሌ ዳዋ<br>• ዋቤ ሸበሌ<br>• ኦጋዴን | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ | • በጎርፍ ሆነ በደለል ስጋት አለ መኖር<br>• የውንዞች ይውሃ አቅም መጎልብት | • ዝቅተኛ የው ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ አጥረት<br>• ከፍተኛ ትነት | • የሚገኘው መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል |